# ዓባይን የመጠቀም መብታችንን የሚነፍገን ህግ የለም!

ፍሬው ተካልኝ 01/30/14

ሀገራችን ለረጅም ዘመናት ከጉያዋ ከሚመነጨው የዓባይ ወንዝ እንዳትጠቀም ቀስፎ የያዛት ስር የሰደደ ድህነቷ እንጂ ወንዙን ሰማንያ አምስት ከመቶ ስትጠቀምበት የኖረችውን ግብጽ በመፍራት እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ አንዲት ሀገር የገዛ ወንዟን የመጠቀም መብት የሚከለክል አንዳች ዓለም አቀፍ የውኃ አጠቃቀም ህግ የለም፡፡ ለዘመናት አንቆና ቀስፎ የያዘን አስከፊ ድህነታችን እንኳንስ ዓባይን ያህል ለታላቅ የልማት ፕሮጀክት የሚውል ወንዝን ልንገድብ ይቅርና እዚህ ግባ ሊባሉ የማይችሉ የልማት ስራዎች ለመከወን የተቸገርን መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡

የዓለም የስልጣኔ ባለቤት የነበርን ህዝቦች በልማቱ ኋላ ቀርተን መታየታችን ታላቅ ሃፍረት ነው፡፡ ለምን ቢሉ ድህነትን ያህል አስከፊና አሳሳቢ ጉዳይ ባለመኖሩ ነው። በታሪክ የሚነገረው የስልጣኔ ባለቤትነታችን እንዴት እንደከሰመ ምስጢሩን ለማወቅ ከባድ ቢሆንም፤ ቀደም ሀገሪቱን ሲያስተዳድሩ የነበሩ ነገስታትና ፊላጭ ቆራጭ አምባገነን መሪዎች ተጠያቂ ለመሆናቸው ግን አያጠያይቅም፡፡

የዓባይ ወንዛችንን ለዘመናት በዘፈን እንጉርጉሮ ከማወደስና ከመርገም በቀር ምንም ሳንፈይድለት ኖረናል፡፡ በእጃችን ያለውን ወርቅ ሳናጌጥበት ለዘመናት ዘልቀናል፡፡ ዓባይ የበረሃው ሲሳይ ከመሆን አልፎ ለእኛ ምናችንም አልነበረም፡፡ በዓይናችን እየተመለከተው የቁልቁል ተፋሰስ ሀገሮች ከመጥቀም በላይ አፈራችንንና ማዕድናችንን ለእነዚህ ተፋሰስ ሀገራት እየገበረ ዘመናትን ተሻግሯል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም በየወቅቱ የግብፅን መንበረ-ስልጣን የሚቆናጠጡ መሪዎቿ ሀገራችን የገዛ ወንዟ እንዳትጠቀም የተለያዩ እኩይ ሴራዎችን ሲከውኑ መኖራቸው የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ይህ ወንዙን በብቸኝነት የሚጠቀሙበት አሮጌ ስትራቴጂ ግን የአሁኑ ትውልድ መሪዎቻቸው ድረስ መሻገሩን ከሰሞኑ የሀገሪቱ መሪዎች 'በዓባይ ወንዝ ላይ ያለንን ታሪካዊ መብት ለማስጠበቅ ጉዳዩን ወደ መንግስታቱ ድርጅት እንወስደዋለን' ካሉት አስገራሚ አባባል ለመገንዘብ አያዳግትም– ኢትዮጵያ በወንዙ ለብቻዋ የመጠቅም ፍላጎት ያላት በማስመሰል ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማደናገር በመሞከር።

እርግጥ በሀገራችን የውጭ ጉዳይና ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የዓባይ ወንዝ አጠቃቀምን በተመለከተ የግብጽ መሪዎች የነበራቸውና ያላቸው አመለካከት በማያሻማ ሁኔታ ተገልጿል፡፡ ይኸውም ኢትዮጵያ በማያባራ ጦርነት ከተናጠች በልማቱ ላይ ማተኮር አትችልም፣ በድህነት ስለምትሰቃይ ለመልማት ብትፈልግም እንኳን አይሆንላትም። ስለሆነም በውኃው ሳትጠቀም ትኖራለች የሚል አስገራሚ እሳቤ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ኋላ ቀር አስተሳሰባቸውን እውን ለማድረግ በየጊዜው የሀገሪቱን መንበረ ስልጣን የሚቆናጠጡ መሪዎች ሀገራችን የዓባይ ወንዝን እንዳትጠቀም የተለያዩ ስትራቴጂ ነድፈው ሲንቀሳቀሱ መቆየታቸው አይዘነጋም–ምንም እንኳን ጠብ ያለ ነገር ማምጣት ባይችሉም።

የውጭ ጉዳይና ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂው የአባይ ወንዝን አጠቃቀም አስመልክቶ እንደሚተነትነው፣ የግብጽ መሪዎች ሀገራችን ወንዙን በለተይም ለመስኖ ልማት እንዳትጠቀምበት ባለ በሌለ አቅማቸው ሲረባረቡ ቆይተዋል፡፡ በገዛ ወንዟ እንዳትጠቀም እንደ ምክንያት የሚያነሱት ደግሞ፣ ወንዙን መጠቀም ከጀመረች ግብጽ ለከፍተኛ አደጋ ትጋለጣለች ከሚል መሰረተ-ቢስ ስጋት የመነጨ ነው፡፡ በዚህም እ.አ.ኤ በ1959 ዓ.ም ግብፅ ከሱዳን ጋር ያደረገችው ስምምነት ውኃውን ሁለቱም ተከፋፍለውት ሲያበቁ፣ ወንዙ 85 ከመቶ የሚፈስባት ሀገራችን አንድም ሊትር መጠቀም እንዳትችል ያደረገ ነበር፡፡ እዚህ ላይ የሚገርመው ነገር ግን በግብፅ መሪዎች አመለካከት ውኃውን ኢትዮጵያ መጠቀም ከጀመረች ግብጽ ትጎዳለች፣ ግብጽ መጠቀም ካለባት ደግሞ ኢትዮጵያ እጅዋን ከውኃው ላይ ማንሳት ይጠበቅበታል የሚል ስትራቴጂ መከተላቸው ነው፡፡ ሆኖም እነዚህን ሁለት አመለካከቶች ስንመለከታቸው እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ጥቅሞች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ግብጾች በአንድ በኩል የዓባይ ውኃ ለሁሉም የማይበቃ አድረገው ሲያዩ፣ በሌላ በኩል ግን እጅግ አባካኝ በሆነ መንገድ ሲጠቀሙበት ይታያሉ፡፡ ለዚሁ በዋናነት ማሳያ ሊሆን የሚችለው በአስዋን ላይ የተገነባው ግድብ፣ በምድረ በዳ ላይ የተገነባና ለትነት በእጅጉ የተጋለጠ በመሆኑ በየዓመቱ ከ10 ቢልዮን ሜትሪክ ቶን በላይ ውኃ በትነት እንደሚባክን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም በተከዜ ወንዝ ላይ በዓመት ከሚፈሰው የውኃ መጠን የላቀ ነው፡፡ ጉዳዩን በዝርዝር ያጠኑ ባለሙያዎች እንደሚያስረዱትም በዓባይ ወንዝ ላይ ያሉ ጥቅሞች በተለይም የኢትዮጵያና የግብጽ ጥቅሞች የሚጣጣሙ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡

ለአብነት ያህልም ኢትዮጵያ በዓባይ ተፋሰስ ላይ ያለውን የተፈጥሮ መመናመን ብታስወግድ፣ በዝናብ እየታጠበ በመሄድ በግብጽና በሱዳን ግድቦች ላይ ደለል እየሞላ

ከፍተኛ ችግር የሚፈጥረውን አፈር መቆጣጠር ትችላለች፡፡ በዚህም ኢትዮጵያና ግብፅ እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበት ዕድል አለ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ሱዳን በየዓመቱ የሚደርስባትን የጎርፍ መጥለቅለቅ ማስወገድ ትችላለች፡፡ እንዲሁም የታችኛው የተፋሰሱ ሀገሮች ርካሽ የኤሌትሪክ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። ውኃው ለትነት በከፍተኛ ደረጃ ስለማይጋለጥም ቢያንስ ሶስት ቢልዮን ኪዮቢክ ውሃ ሊቆጠብና ለተፋሰሱ ሀገሮች ጥቅም ሊውል መቻሉም እንዲሁ፡፡

ታዲያ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ የግብፅ ባለስልጣናት እነዚህ ጥቅሞች ሊጣጣሙ የማይችሉ አስመስለው ኢትዮጵያ የአባይ ወንዝን እንዳትጠቀም ከጠነኛ አመለካከት ያልመነጩ የተለያዩ የተለያዩ ሃሳቦችን ሲያቀርቡ ኖረዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ሀገራችን የአባይ ወንዝን ለልማት እንዳታውለው ከሌሎች ሀገራት ብድርና ዕርዳታ እንዳታገኝ ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ መቆየታቸው አንዱ ነው፡፡ ዛሬም ይህን ጤነኛ ያልሆነ መንገድ እንደሚከተሉ ይፋ አድርገዋል። ግብጽ ቀደም ባሉት ጊዜያት በአረቡ ዓለም ያላትን ተሰሚነት በመጠቀም ሀገራችን የአባይ ወንዝን ለማልማት እንዳትችል ከሌሎች የአረብ ሀገራት ምንም ዓይነት ብድርና ዕርዳታ እንዳታገኝ የማድረግ ስትራቴጂዎችን ብትቆይም ትናንት ዛሬ አለመሆኑን የተረዳችው አትመስልም፡፡

እርግጥም የግብጽ ባለስልጣናት ሲከተሉት የቆዩትና ዛሬም ጊዜያዊ መንግስቷ የሚያቀነቅነው ያረጀና ያፈጀ እሳቤ ዛሬ ላይ አይሰራም። ዛሬ ያለችው የትናንቷ ኢትዮጵያ አይደለችም። ዛሬ ሀገራችን የማንንም ዕገዛ ሳትሻ ህዝቦቿን በማስተባበር ዋና ዋና የልማት ትልሞችን በራሷ አቅም የማከናወን አቅም አላት–ምስጋና የህዝቦችን ተጠቃሚነት ከፍ በማድረግ የሀገሪቱን ምጣኔ ሃብት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠቃሽ እንዲሆን ላደረጉት የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ይሁንና።

በአሁኑ የህዝቦችን የልማት አስተሳሰብ በእጅጉ ተለውጧል፡፡ ዛሬ 'እናንተ በወንዛችሁ የመጠቀም መብት የላችሁም' የሚለው የግብጾች የቅዥት ጉዞ ያበቃለት ነው ማለት ይቻላል። በሀገራችን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ተገንብቶ ውጤታማ እየሆነ ነው። ይህ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት የህዝብን ተሳትፎ በሚያረጋግጡና ዋጋ ባላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እየተመራ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ወደፊት እንዲራመድ እያደረገ ነው፡፡ በዚህም በህዝብ ተሳትፎ የሚገነቡ ታላላቅ ፕሮጀክቶች በመገንባት ላይም ይገኛል፡፡ ለዚሁ ታላቅ አብነት የሚሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ

ግድብ ግንባታ ነው፡፡ በአንድ ወቅት አንቀላፍተን የነበረን ህዝቦች አሁን ልማታዊ መንግስታችን በፈጠረው መነቃቃት ከእንቅልፋችን ነቅተን ያንን የቀድሞ ስልጣኔያችንን ለመመለስ በአዲስ መንገድ ጎዞ ጀምረናል፡፡

የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለዘመናት በድህነት አረንቋ ሲዳክሩ የነበሩት ምርጫቸው ሆኖ አይደለም– በየወቅቱ ሀገራችን ያስተዳድሯት የነበሩት መሪዎች ስልጣናቸውን ከማደላደል በሰቀር ለህዝቦች የሚጠቅም ፖሊሲና ስትራቴጂ መንደፍ ስለተሳናቸው እንጂ፡፡ እነዚህ ቀደምት ንጉሳዊና አምባገነን መሪዎች ህዝቡን ለዕድገትና ለብልጽግና ከማነሳሳት ይልቅ፤ ተግባሮቻቸውን ሁሉ የሚለኩት ለስልጣናቸው የዕድሜ ማራዘሚያነት ካለው ፋይዳ አኳያ ብቻ ነበር። ዛሬ ግን ቀደም ሲል የጠቀስኩት ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሰት ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርጉና በተግባር ውጤታማ የሆኑ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ነድፎ በውጤቱም እንደ ማንኛውም ኃላፊት እንደሚሰማውና ለህዝብ እንደሚቆረቆር መንግስት ታላላቅ ግድቦችን ጨምሮ ሌሎች በዓይን የሚታዩ ልማታዊ ክንዋኔዎችን እየፈፀመ ነው።

እንደሚታወቀው በዓለማችን ላይ በርካታ የወንዝ ግድብ ፕሮጀክቶች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊት የግንባታ ፕሮጀክቱ ከተጀመረችውን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ጋር እኩል ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት ኃይል የሚያመነጨውንና እ.ኤ.አ. በ1972 የተጠናቀቀው የሩሲያው ክራስኖሻርስከያን ግድብ መጥቀስ ይቻላል። ይህ ግድብ በዓለማችን በሰባተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ቅሉ፤ በግንባታው ወቅት ሩሲያ በውሃ ሃብቷ እንዳትጠቀም የከለከላት አንዳችም ህግ አልነበረም፤ ሊኖርም አይችልም። ለነገሩ አንድ ሀገር በገዛ የተፈጥሮ ሃብቷ የመጠቀም መብት የላትም የሚል ዓለም አቀፍ የውኃ አጠቃቀም ህግ የለም፡፡ እንዲህ ዓይነት ህግ ቢኖር ኖሮ፤ ሀገሮች ወንዛቸውን ገድበው የገነቧቸውንና ዛሬ በዓለማችን የተገነቡ ታላላቅ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ፕሮጀክቶችን ባልተመለከትን ነበር፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን ሀገራችን በተፈጥሮ ሃብቷ የመጠቀም መብቷን ወደ ተግባር በመለወጥ የህዳሴውን ግድብ ጀምራለች። ስራውም በብድርና በዕርዳታ ሳይሆን በኢትዮጵያ ህዝብ አንጡራ ሃብት በከፍተኛ ፍጥነት እየተከናወነ ነው። በቅርቡ የወጣው ሪፖርት እንደሚያመለክተው የፕሮጀክቱ የስራ ሂደት ሰላሳ በመቶ መጠናቀቁን ይፋ አድርጓል፡፡ ግና ይህ ሪፖርት ለግብጽ ባለስልጣናት ራስ ምታት ሆኖባቸው ሰንብቷል፡፡ በውስጣዊ

ፖለቲካዊ ቀውስ እየታመሰች ያለችው የግብጽ ባለስልጣናቷ ያገራቸውን ችግር ከመፍታት ይልቅ የችግራቸውን ጡዘት አቅጣጫ ለማስቀየር ፊታቸውን ወደ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ አዙረዋል። እርግጥ የግብጽ ባለስልጣናት በአባይ ወንዝ ላይ ያላቸው አመለካከት ዛሬ የፈጠሩት ሳይሆን ከቀደምት መሪዎቻቸው የወረሱት በመሆኑ ዛሬም ይህን ጉዳይ እንደ ፖለቲካ ትኩሳት ማብረጃ መጠቀማቸው የሚገርም አይደለም፡፡

ይሁንና በአሁኑ ወቅት የኢፌዴሪ መንግስት የህዳሴው ግድብ ግንባታ ሰላሳ ከመቶ ተጠናቋል ብሎ ይፋ ማድረጉ በግብጽ ባለስልጣናት በኩል ሁለት ዓይነት አመለካከቶች እየተንፀባረቁ ይገኛሉ፡፡ በህዝባዊ ምርጫ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት መሐመድ ሙርሲን ከመንበረ ስልጣናቸው ከተወገዱ በኋላ ስልጣኑን የተረከቡት ፕሬዚዳንት መንሱር አድሊ የህዳሴው ግድብ ሰላሳ ከመቶ ስራው ተጠናቅቋል መባሉ ከእውነት የራቀ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡ እንዲያውም ከየት እንዳመጡት ባይታወቅም ፕሮጀክቱ የፋይናንስ እጥረት እንደገጠመውም ገልፀዋል፡፡ እርግጥ ይህ የፕሬዚዳንቱ አስተያየት ከምንም የመነጨ ማለት አይቻልም። ምክንያቱም ጊዜያዊ ፕሬዚዳንቱ እንዲህ ዓይነቱን መሰረት አልቦ አባባልን ማናገር የፈለጉት በሀገራቸው በመካሄድ ላይ ያለውን ህዝባዊ አመፅ ለማረጋጋት ያስችላል የሚል አመለካከት ስላላቸው መሆኑ ግልፅ ስለሆነ ነው፡፡

ሌላኛው በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ አስተያየት የሰጡት የግብጽ ባለስልጣን የግብጽ የውኃና ማዕድን ሚኒስትር ናቸው፡፡ እርሳቸውም የኢትዮጵያ መንግስት እየገነባ ያለውን ፕሮጀክት ለግብጽ ትልቅ ጉዳት ስለሚያስከትል በአስቸኳይ መቆም አለበት ባይ ናቸው— ማሳሰቢያ አይሉት ትዕዛዝ ዓይነት ነገር፡፡ ታዲያ እነዚህ ሁለት የግብጽ ባለስልጣናት የሰጡትን አስተያየት የተመለከትን እንደሆነ እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ አንደኛው ግድቡ በፋይናንስ እጥረት የሚካሄድ አይደለም ሲል፣ ሌላኛው ደግሞ የሚካሄደው ግንባታ ግብፅን ስለሚጎዳት ባስቸኳይ መቆም አለበት የሚል ነውና። ዳሩ ግን የግብጽ ፖለቲከኞችና ባለስልጣናት በየፊናቸው የህዳሴ ግድቡ አስመልክተው የሚሰጧቸውን የተምታቱ መግለጫዎችን ተከትሎ የኢትዮጵያ መንግስትም ምላሽ ሰጥቷል፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ከግብጻውያን እየተዘነዘሩ ላሉት ከእውነት የራቁ ዘገባዎች አስመልክተው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ዲና ገለጻ፣ ግብጽ ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ እየገነባች ያለውን የህዳሴ ግድብ ግንባታ እንዲቋረጥ እያደረገችው ያለውን ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ

ጥረት ኢትዮጵያ እንደማትቀበለውና የግድቡ ግንባታም ለየትኛውም ተፋሰስ ሀገራት ላይ ምንም ጉዳት እንደማያደርስ ኢትዮጵያ አሁንም ጥረቷን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለማስገንዘብ ሰፊ ስራ ታከናውናለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግብጽ ፕሮጀክቱ እንዲቋረጥ እያካሄደች ያለውን የማጥላላት ዘመቻ በመፍራት የህዳሴ ግድብ ለአንድ ደቂቃ ይቋረጣል ብሎ መመኘት የዋህነት ነው ብለዋል፡፡

የግብጽ ፖለቲከኞች ዘመቻ ታዋቂ ሰዎቻቸውን በመጠቀም በየእምነት ተቋማትና በተለያዩ ህዝብ የሚሰበሰብበት አካባቢዎች ታላቁ ህዳሴ ግደብ ግንባታ በግብጽ ላይ ከፍተኛ ስጋት የሚያደርስ ስለሆነ ፕሮጀክቱ መቋረጥ ይገባዋል የሚል አቋም ይዘው እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ ይህ ተግባራቸውም በግብጽ ውስጥ ላሉ ዜጎች ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎች ሀገራት በስደት ላይ ለሚገኙ ግብጻውያንም ጭምር በተንሸዋረረ መንገድ እየተነገረ ነው፡፡

ግብፆች የህዳሴውን ግድብ በህገ-መንግስታቸው ጭምር ከማውገዝ አልተቆጠቡም። እንደሚታወቀው በታህሪር አደባባይና በሌሎች ቦታዎች ህዝባዊ አመፅ ያልበረደባት ግብጽ፤ ቀደም ሲል በምርጫ ስልጣናቸው የጨበጡት ፕሬዚዳንት መሐመድ ሙርሲ ከስልጣን ከተወገዱ በኋላ ሰሞኑን አዲስ ህገ - መንግስት አርቅቃ መጽደቋ ይታወሳል፡፡ ይኸው ህገ-መንግስት በአንቀጽ 44 ላይ ስለ አባይ ወንዝ ይደነግጋል– የግብጽ መንግስት የውኃ ብክነትንና ብክለትን መጠበቅ፣ በወንዙ ላይ የሚካሄዱ ሳይንሳዊ ምርምሮችን መደገፍ፣ የሀገሪቱን ታሪካዊ የውሃ ባሌበትነትንና የመጠቀም መብትን ማስጠበቅ እንደሚገባው በመግለፅ፡፡

ታዲያ ለዚህ አዲስና አስገራሚ ህገ-መንግስት አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ምላሽ ሰጥተዋል– ግብጽ አዲስ ህገ - መንግስት አርቅቃ ማጸደቋን ኢትዮጵያ እንደምታደንቅ፣ ነገር ግን አንዲት ሀገር ህገ - መንግስት ስትቀርጽ የሌሎች ሀገራትን መብትና ጥቅም በጠበቀ መልኩ መሆን እንደሚገባው አስምረውበታል፡፡ በአንድ ወቅት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ከአሶሼትድ ፕሬስ ጋዜጠኛ ጋር ያደረጉትን ቃለ - ምልልስ አምባሳደሩ አስታውሰዋል። ጋዜጠኛው ጠቅላይ ሚኒስትሩን 'ግብጽ ኢትዮጵያን ብትወር ምን ታደርጋላችሁ?' የሚል ጥያቄ አቅርቦላቸው እርሳቸውም 'ከዚህ በፊት ሀገራችን የወረሩ አባቶቻቸው በጊዜው የሆነውን ታሪክ ተመልሰው ለመንገር የቻሉ አልነበሩም፡፡ የአሁኑ ፖለቲከኞችም ይህን የሚዘነጉት አይመስለኝም' በማለት ምላሽ መስጠታቸውን በመግለፅ፡፡

ይህም ግብፆች ማናቸውንም ተግባራት ለመፈፀም ለማስፈራራት ቢሞክሩም የማይሳካላችው መሆኑን የሚያመላክት ነው። ይሁንና ከመሰንበቻው የግብጽ የውኃ ሀብት ሚኒስትር ቃል አቀባይ ካሊድ ዋሊፍ ለአል-ሞኒተር አንድ አስደማሚ ነገር ተናግረዋል– የህዳሴው ግድብ ተጠናቅቆ ዕውን ከሆነ በግብጽ ላይ ጉዳት ስለሚያደርስ ጉዳዩን ወደ ሚመለከተው አለም አቀፍ ተቋም እንደሚወስዱትና ለዚህም አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረጉ መሆናቸውን በማስታወቅ፡፡

ታዲያ ቃል አቀባዩ ካነሱት ሃሳቦች መካከል ግብጽ ለጋሽ ሀገራት ለኢትዮጵያ የሚያደርጉት ዕርዳታ ለማስቆም እንቅስቃሴ እናደርጋለን፣ በ1929ና በ1959 እ.ኤ.አ እንግሊዝ፣ ኬንያ፣ ታንዛንያና ኡጋንዳን በመወከል ከግብጽ ጋር በአባይ ጉዳይ ላይ የተፈራረመችው ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን ታሪካዊ ባለቤትነታችን አንስተን ወደ ዓለም አቀፍ ተቋማት በመሄድ እንከራከራለን የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡ ሆኖም በዚህ ጉዳይ የኢትዮጵያ የውኃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ቶፊቅ አህመድ ለሀገር ውስጥ ሚያዲያዎች ሰሞኑን በሰጡት መግለጫ፤ ኢትዮጵያ የቅኝ ግዛት ውሉ እንደማይመለከታትና ውሉን እንደማትቀበለው አስታውቀዋል። የ1929ና የ1959 የቅኝ ግዛት ውል በአዲሱ ሁለገብ የውኃ አጠቃቀም (CFA) በተፋሰሱ ስድስቱ ሀገሮች ፊራሚነት መተካታቸውንና ህግ ሆኖ መጽደቃቸውን በማስታወስ፡፡

እርግጥ እዚህ ጋር ሊነሳ የሚገባው አንድ ጥያቄ አለ። እርሱም የግብጽ ፖለቲከኞችና ባላስልጣናት ስድስቱ ተፋሰስ ሀገራት ሙሉ በሙሉ ያፀደቁትን ስምምነት ከመቀበል ይልቅ፤ ኢትዮጵያ የቀኝ ተገዥ ሀገር ባለመሆኗ ያልፈረመቻቸውን የ1929 እና የ1959 ስምምነቶችን ይከበሩልኝ የሚለውን ነገር ማንሳት ለምን አስፈለጋት? የሚለው ነው። እንደሚታወቀው የአባይ ወንዝ 56 ቢሊዮን ሜትሪክ ኪዮብ ውሃ ነው፡፡ የተፋሰሱ ሀገራት ደግሞ አስር ናቸው፡፡ ከዚሁ ውስጥ ግብጽ 21 ቢሊዮን ኪዮቢክ ውሃ ይገባኛል በማለት ክርክር እያነሳች ነው፡፡ የግብጽ አስተሳሰብ በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ውኃውን እናንተ አትንኩት እኔ በብቸኝነት ልጠቀምበት ከሚል ግለኝነት የመነጨ ነው፡፡

ለነገሩ በማናቸውም ወቅት በግብጽ ውስጥ ስልጣን የሚይዙ መሪዎች የዓባይ ጉዳይ የመጀመሪያ አጀንዳቸው አድርገው እንደሚመለከቱት ይታወቃል፡፡ አሁን በግብጽ ያለው መንግስትም ቢሆን የፕሮጀክቱ ሂደት እንዲቋረጥ መወትወቱን ቀጥሏል፡፡ ዳሩ ግን

የጥያቄው መነሻም ሆነ መድረሻ የህዳሴው ግድብ በግብፅ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርስ መሆኑ አይደለም– በሀገሪቱ ላይ እየተቀጣጠለ ያለውን ህዝባዊ አብዮት ለማብረድና ውስጣዊ የፖለቲካ ችግራቸውን ለመሸፈን ያለመ እንጂ፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን እዚህ ላይ 'ዕውን ግብጽ ኢትዮጵያ እያከናወነች ያለውን የህዳሴ ግድብ ግንባታ ማስቆም ትችላለችን?' የሚል ጥያቄን ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል። ይሁንና ይህ አስተሳሰብ ፍጹም የማይታሰብና ምንም ዓይነት መሰረት የሌለው መሆኑን ሁለት ጉዳዮችን በመጥቀስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንደኛው የግድቡ ግንባታ በትክክል በግብፅ ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ ካይሮ ምንም ዓይነት ሳይንሳዊ ትንታኔ መስጠት የማትችል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ማንም ሀገር የገዛ ወንዙን ሌሎችን በፍትሃዊነት ተጠቃሚ በሚያደርግበት ሁኔታ የመጠቀም መብት የለውም በማለት ተከራክረው የሚያስሙኑበት ህግ አለመኖሩ ነው። አዎ! እነዚህ ዕውነታዎች የግብጾችን ጩኸትና ፉከራ ባዶና ትርጉም አልባ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ምንም እንኳን ግብፆች መሰረት አልቦ ክርክር ለማስነሳት ቢሹም፤ ለውድ አንባቢዎቼ ስለ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ተጨባጩን ሃቅ ማሳወቅ የግድ ይላል። እናም የግድቡ እውነታዎች ሲዳሰሱ ይህን ይመስላሉ።…ፕሮጀክቱ ሶስት ዓመታት ሊያስቆጥር የቀሩት ሁለት ወራቶች ብቻ ሲሆኑ፤ በእዚህ ጊዜያት ውስጥም ሰላሳ በመቶ ስራው ተጠናቅቋል፡፡ ግድቡ በአህጉራችን ቀዳሚው ሲሆን፤ በዓለማችን ደግሞ ስራውን ሲጠናቀቅ ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት በማመንጨት የሰባተኛ ደረጃን ይይዛል፡፡ ግድቡ በአጠቃላይ 16 ተርባይኖች ሲኖሩት፤ አስሩ በግራ ስድስቱ ደግሞ በቀኝ በኩል ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ተርባይኖች እያንዳንዳቸው 350 ሜጋ ዋት ያመነጫሉ፡፡ በነገራችን ላይ በመጪው ዓመት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል የሚከበረው የህዳሴው ግድብ ግንባታ በሚካሄድበት አካባቢ ነው፡፡ እናም ያኔ ከ16ቱ ተርባይኖች ውስጥ ሁለቱ ተርባይኖች ለሀገራችን ሰባት መቶ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል ይሰጣሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

የፕሮጀክቱ የሲቪል ምህንድስና ስራ በጣሊያኑ ሳሊኒ ኮንስትራክሽን አማካኝነት እየተካሄደ ሲሆን፤ የሃይድሮ ኤሌትሪክና ኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራው ደግሞ በኢፌዴሪ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ሀገር በቀሉ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ይህን መሰሉን ታላቅ ስራ ሲያከናውን የመጀመሪያው ቢሆንም፤

ግድቡ ሲጠናቀቅ ከቴክኖሎጂ ሽግግር አንፃር ጠቃሚ ልምድ እንደሚያገኝ ይታመናል። በግድቡ ከ6500 መቶ በላይ ኢትዮጵያዊያን ስራተኞች የስራ ዕድል አግኝተዋል፡፡ ይህም ግድቡ ለዜጎች ስራ በመፍጠር ረገድ የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከሌሎች በዓለማችን ከተገነቡ ግድቦች ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር ህዝቡ የራሱን አሻራ ያሳረፈበት ፕሮጀክት መሆኑ ነው፡፡ እናም ፕሮጀክቱ ህዝቦች በልማቱ ላይ ያላቸውን አስተሳሰብ በአንድ እስትንፋስ ያስተሳሰረ ሆኗል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ከዚህ ቀደም በሀገራችን ታሪክ የነበሩት መንግስታት ያልደፈሩትን የዓባይ ወንዝ እንዲገደብ ያከናወነው ተግባር የሚደነቅ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም ቢሆን መንግስት መላውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔሰቦችና ህዝቦች ባሳተፈ መልኩ የግድቡ ግንባታ እያስቀጠለ ይገኛል፡፡

በአንጻሩ ግን ግብጾች የፕሮጀክቱ ሂደት እንዲቆም መያዣና መጨበጫ የሌላቸውን አሮጌ ስምምነቶችን በመጥቀስ ውትወታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ነገር ግን እኛ አረቦች “ውሾቹ ይጮሃሉ፣ ግመሎቹ ግን ጉዟቸውን ቀጥለዋል” እንዲሉ፤ የህዳሴ ግድባችንን እንደጀመርነው በማጠናቀቅ ለሌላ የልማት ታሪክ መዘጋጀት ይኖርብናል፡፡ የተፈጥሮ ሃብትህን ፍትሐዊና ሌሎችን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ አትጠቀም የሚል ምንም ዓይነት ዓለም አቀፋዊ ህግ የለምና።